# የነጻነት ድምፅ
# The Voice of Freedom

በወቅታዊ አርዕስት በአፋብን የፖለቲካ መምሪያ እየተዘጋጀ የሚቀርብ
Issued by AFNM Political Department on Current Topics
ጽሁፍ ለመላክ → contributions@thevoiceoffreedom.net ← for contributions
በኢንተርኔት ለማንበብ→ https://thevoiceoffreedom.net ← read online

Vol. 1; No. 1
አንደኛ ዓመት አንደኛ እትም

Saturday, September 05, 2026
ቅዳሜ ነሐሴ ፴ ቀን ፳፻፲፰ ዓ.ም.


## ርዕሰ አንቀጽ

## Editorial

### ከሀገሪቱ ርዕሰ መዲና እስከ ገጠር ቀበሌ የተቀናጀው መንግስት መር ሀገር የማፍረስ እንቅስቃሴ፡

ድምጻዊ ዓለማየሁ እሸቴ በሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደ የዘመን መለወጫ በዓል ላይ፤ ወደ መድረክ ወጥቶ መዝፈን ሲጀምር አዳራሹ በሙሉ በታላቅ ጭብጨባ ተቀበለው። በወቅቱ ድምጻዊ ዓለማየሁ እሸቴ፤ በጨካኙ ዐብይ አሕመድና ጋሻጃግሬወቹ ፊት ይዘፍን የነበረው፤ ‹‹አዲስ አበባ ቤቴ›› የሚለውን ዘመን አይሽሬ ዘፈን ነበር። ድምጻዊ ዓለማየሁ እሸቴ በዘፈኑ፤

*"አዲስ አበባ ቤቴ አዲስ አበባ ቤቴ፤*
*ቆንጆ ልጅ ሸጋ ልጅ አለች ጎረቤቴ፤*
*ኧረ እንዲያው ይመኙሻል፤*
*ኧረ እንዲያው ይመኙሻል፤*
*በምኞት ቢጓዙ ወዴት ያገኙሻል?"*

ይላል።

ይህን ዘፈን ድምጻዊው መዝፈን ሲጀምር ነበር በአዳራሹ የነበረው ታዳሚ፤ ዘፋኙን በደስታና በጭብጨባ እንዲቀበለው ያስገደደው። ታዳሚው በዚህ ስሜት እንዲገባ ያደረገው ደግሞ፤ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም በኢትዮጵያ ስም ቃለ መሀላ የፈጸመው ጨፍጫፊው ዐብይ አሕመድ፤ ገና ሥልጣን ከመያዙ ስግብግብ የተስፋፊነት ድርጊቱን መፈጸሙን ተከትሎ የከተማው ህዝብ፤ የመወረርና የመበተን ስጋት ስለገባው ነበር።

ዛሬ ድምጻዊው ወደፈጣሪው ሄዷል፤ በድምጻዊው ዘመን ተሻጋሪ ዘፈን ስሜቱን መቆጣጠር ተስኖት ደስታውን በእምባ የገለጸው ታዳሚ ደግሞ፤ ከሚወዳት ከተማውና ካደገበት ቀየው ግማሹ በአካል ሌላው ደግሞ በስነ-ልቦቦ ተፈናቅሎ ባይተዋር ሆኗል። ‹‹ከዳር አስወጡት፤ መሀል ገቡና›› እንዳለው ዘፋኙ ማለት ነው። በአሁኑ ሰዓት ከሰባት ሚሊዮን በላይ የሚሆነው የአዲስ አበባን ህዝብ አናውቅህም የሚል መንግስት ተፈጥሯል። በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ጭንብል የተሸፈነው ይሄኛው የኬኛ ፕሮጀክት አይን ያወጣ የወረራ እና የተስፋፊነት ማስፈፀሚያ እንጅ ስለ የጋራ ሀገር፣ ችግር ስለመፍታት፣ ሕዝብን ስለመጥቀም ቅንጣት እሳቤ እንደሌለው በተግባር አሳይተዋል።

በእርግጥ አገዛዙ አዲስ አበባ ላይ እኩይ እቅዱን ማስፈጸም የጀመረው፤ ‹‹ከተማ ማስዋብ›› በሚል ማደናገሪያ ነበር። ‹‹ገበታ ለሸገር፤ አንድነት ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ ወዘተ›› ብሎ ታሪካዊውን የምኒልክ ቤተ መንግሥት የድኩላና የዘንባባ ፓርክ በማድረግ የጀመረውን አሻራ የማጥፋት ዘመቻውን፤ ‹‹የኮሪደር ልማት›› በሚል ሌላ ማደናገሪያ፤ የከተማዋን ነባር ነዋሪዎች ለማፈናቀልና ለመበተን የታቀደ ነው።

የከተማን መዋብና ማማር የሚጠላ ማንም የለም። የአማራ ሕዝብ የህልውና ትግል መዳረሻ ግቡም፤ መላው የአገራችን ሕዝብ በተመቻቸ አካባቢያዊ ሁኔታ በደስታና በሰላም ተረጋግቶ እንዲኖር ነው። ነገር ግን



**ምስል ፤** *በ1879 ዓ.ም በዳግማዊ አጤ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ተቆርቁራ ላለፉት 140 አመት የኢትዮጵያ መዲና እና የአፍሪካ የዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችው አዲስ አበባ (ብሔራዊ ባንክ አካባቢ)።*

የዐብይ አሕመድና የቡድኑ ዓላማ፤ በኮሪደር ልማት ስም የሚፈጽመው ሸፍጥ አገርና ታሪክ ማፍረስ ነው። ሂደቱ በተጠና፣ በታቀደ እና በስልታዊ መልኩ የሚከናወን አዲስ አምባገነንነትን የማዋለድ የጨፍላቂነት እቅድ ነው። ይህ ከተማ የማስዋብ ፕሮጀክት ህዝቡ ለዘመናት የገነባውን የአብሮነት እሴት በመናድ እንዳይደጋገፍ በማፈናቀል እንዲበታተን ተደርጓል፣ ይህም አዲስ አበባ ላይ ለታሰበው ሴራ ቤተ-ሙከራ መሆኑ ነበር።

የነባሩን ህዝብ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ትስስር ማፍረስ፤ በልማት ስም በከተማዋ መሀል የሚገኙ እንደ ፒያሳ፣ አራት ኪሎ፣ ካዛንቺስ እና መርካቶ ያሉ ነባር ሰፈሮች በግፍ እንዲፈርሱ ሲደረግ፤ አብዛኛው ነባር ነዋሪ በተለይም የአማራና የሌሎች ህዝቦች ተወላጅ የማህበራዊ ትስስሩ እንዲበጣጠስ እና ወደ ከተማዋ ዳርቻዎች እንዲበታተን ተደርጓል።

ከየትኛውም የኢትዮጵያ የገጠር ጫፍ እንኳን ብንወስድ አዲስ አበባ (ገጽ 2 ላይ ይቀጥላል)

### The Integrated State-Led Campaign to Dismantle the Nation: From the Capital to Rural Kebeles – a summary

Addis Ababa belongs to its residents. In addition, the issue of Addis Ababa is the issue of all Ethiopians. Rather than building upon our shared national values, the past few regimes have been working sleeplessly to divide our national assets and heritage—built together through immense sacrifices in the past—like meat cut-up for sharing. We stand as Ethiopia through the Addis Ababa we built together, and through Adwa, where we shed our collective blood and bone to accomplish a heroic feat that astonished the world. We stand through the flag for which we fell together at Karamara.

(continued on page 4)

### "የነፃነት ድምጽ/ The Voice of Freedom" አጭር መግለጫ!

#### የመጽሔቱ አላማ፤

የነፃነት ድምጽ/ The Voice of Freedom/ የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ – ይፋዊ የፖለቲካ ልሳን ነው። አላማውም የአማራ ሕዝብ ለህልውናው፣ ለፍትህ እና ለብሔራዊ ክብሩ የሚያደርገውን ህዝባዊ ትግል፤ በየሳምንቱ በሚታተም መጽሔት በፖለቲካ፣ በሃሳብ እና በመረጃ የበለፀገ ማድረግና የድርጅቱንና የሕዝቡን የትግልና የፖለቲካ መስተጋበር ከፍ ለማድረግ ነው። መጽሔቱ የንቅናቄውን መስመር፣ በየምዕራፉ የሚደረስባቸውንና የሚጠይቀውን ተሳትፎ ለታጋዮች፣ ለደጋፊዎችና ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተዳራሽ በማድረግ የአማራን የሕልውና ትግል ደጋፊ ማሳደግን ያለመ ነው።

(ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል)

### የ2019 የትምህርት ዘመንን በተመለከተ ከአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ ማሕበራዊ ጉዳዮች መምሪያ የተሰጠ አቅጣጫ!

ዘረ-ፈጁ አገዛዝ ከክልሉ ውጭ ያለውን አማራ በመጨፍጨፍ ከነበረበት ቀየው ሚሊዮኖችን ካፈናቀለ በኋላ በተለያዩ ካምፖች ታጉረው "የነገ እጣፈታቸው የማይታወቅ" ከሚባል መዝገብ ውስጥ እንዲካተቱ አድርጓቸዋል።

(ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል)

## ከሀገሪቱ ርዕሰ መዲና እስከ...

(ከገጽ 1 የቀጠለ)

ዘመድ የሌለው ማግኘት በፍጹም አይታሰብም:: ስለዚህ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያስበው ከተማዋ፣ የሀገሩ መዲና፣ የቅርብ ዘመዱ መገኛ፣ የነጻነት መቦረቂያ፣ የሁሉ ነገር መሸመቻ፣ የስልጣኔ ማማ፤ የአፍሪካ መቀመጫ ናት፤ አዲስ አበባ:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፣ አዲስ አበባ ታማለች፤ መላ ኢትዮጵያዊ ታሟል:: ዘረፈጁ ዐብይ አሕመድ የጥፋት ዳመናውን አጥልቶባታል፤ መዋቅራዊ ከበባ (The Structural Siege) ውስጥ አስገብቷታል:: አዲስ አበባን በዙሪያዋ በሚገኙ አፍራሽ ፕሮጀክቶች ከቦ "ሸገር ከተማ" በሚል አዲስ መዋቅር ስር ማደራጀቱ፤ የከተማዋን ተፈጥሮአዊ እድገት ለመግታት፣ የመሬትና የፖለቲካ ቁጥጥሩን ለአንድ ወገን ለማስረከብ የተደረገ የታቀደ መዋቅራዊ ከበባ ነው:: የከተማዋን ታሪካዊ ህብረ-ብሔራዊ ማንነት በመሰረዝ፣ በትምህርት ቤቶች እና በተቋማት ላይ የቋንቋና የባህል የበላይነትን በግድ የመጫን አካሄድ፣ ነዋሪውን በገዛ መኖሪያው "ሁለተኛ ዜጋ" እና "ባዕድ" የማድረግ ስነ-ልቦናዊ ጦርነት ነው::

ወዲህ ደግሞ፤ በቢዛሞ/ወለጋ ጠቅላይ ግዛት የተፈጸመ እጅግ አደገኛ የሚባልና ከባድ የጦር ወንጀል፤ በዚሁ ጨፍጫፊና ገዳይ አገዛዝ ተፈጽሟል:: የወለጋውን የዘር ማጽዳት ወንጀል ወደፊት በምናወጣው እትማችን በዝርዝር የምንመለከተው ሆኖ፤ ለዛሬው በወፍ በረር ስንመለከተው፤ ይህ ጭካኔ የተሞላበትና ታቅዶ የተፈጸመው የዘር ማጽዳት ዘመቻ የተካሄደው፤ ከአገዛዙ ነፍሰ በላ ሠራዊት በተጨማሪም፤ ‹‹ጥሬ ስጋ እየመገብን ያዘጋጀነው ሠራዊት ነው›› ተብሎ በሽመልስ አብዲሳ የተነገረለት ገዳ ኮማንዶ ሀይል፤ ከክልሉ ሚሊሻ፣ አድማ ብተና እና ሸኔ ጋር ቅንጅት በመፍጠር ነው:: ይህ በቀናት ብቻ ከ500 በላይ የወለጋ አማራን ህዝብ ጾታ፣ ዕድሜ፣ የሥራ ባህሪ ሳይመርጥ፤ በአማራነታቸው ብቻ በመለየት የተገደሉበት ዘመቻ፤ ‹‹በጉልበትና በሀይል የተፈጸመ›› ሲል ይኸው ወንጀለኛ አገዛዝ ገልጾታል::

አማራ ጠል ፀረ ኢትዮጵያ ሀይሎች ከድህረ 1966 ዓ.ም ጀምሮ መንግስታዊ በትራቸውን በአማራ ብሎም በሀገሪቱ የታሪክ፣ የስልጣኔና የአንድነት ምሰሶዎችን ለማፍረስ ተጠቅመውበታል:: ገሚሶቹ በሻገተ ሶሻሊዝም ተከታዮቹ በሌለ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ስም በመደበቅ አማራን ከቆረቆረው ከተማ፣ ከንብረቱ፣ ከቀየውና ከማንነቱ አፈናቅለው ሲያበቁ፣ በገጠር ያለውን ገበሬ ደግሞ ከማሳው፣ በሬውን ከቀንበሩ አፋተው አማራውን ተወልዶ ባደገበት ቀዬ ስደተኛ እንዲሆን ተደርጓል:: ይህን እኩይ የጥላቻ ፖለቲካ፤ ደርግ ፈጽሞታል፣ ኢሕአዴግ ደግሞታል፤ የዐብይ አሕመድ የጭካኔ አገዛዝ ደግሞ ካለፉት ጨካኝ ገዥዎች በከፋ መልኩ እየተገበረው ይገኛል::

ሥልጣኑን በያዘ በመጀመሪያው ስድስት ወር የጋሞ ተወላጅ የሆኑ የቡራዩ ከተማ


ምስል 2፤ አዲስ አበባን በማፍረስ ቤት አልባ የተደረጉ ነዋሪዎች በፒያሳ (ምንጭ፤ The Guardian)።

ነዋሪወችን ስውር ገዳይ ቡድን ልኮ በማስጨፍጨፍ ወንጀሉን ያለማመደን ዐብይ አሕመድ፤ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ፤ ‹‹በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኘው የኦሮሞ አርሶ አደር፤ ጠቅላይ ሚኒስትሬ ተነካ ብሎ፤ አዲስ አበባን እንዳልነበረች ሊያደርጋት ነበር›› ብሎ ሲናገር ሀፍረት አልተሰማውም:: በዚህ ነውርና የጦር ቅስቀሳ ንግግሩ ብቻ ያልተመለሰው ዘረ-ፈጁ ዐብይ፤ ‹‹አዲስ አበባ ውስጥ ከፍተኛ የኦሮሞ ጥላቻ ያለው አስተሳሰብ በዝቷል›› ብሎ መናገሩ አይዘነጋም:: በዚህ መልኩ ፅንፈኝነትንና ገዳይነትን እያለማመደ ያመጣውን ወንጀል በመጨረሻም፤ ከተማ ላይ በአዳራሽ ስብሰባ፤ ክፍለ ሀገር ላይ ደግሞ በተቀናጀ ወታደራዊ ዘመቻ፤ ፍላጎቱን ለማስፈጸም፤ የሄደባቸውን መንገዶች አሳይቷል::

አዲስ አበባ ላይ የፈጸመውን ነውር ያጋለጡ ምሁራን እና የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት መሪዎች፤ እስከ ዛሬ ድረስ ማዋከብና ማሳደድ እየተፈጸመባቸው መሆኑን ተናግረዋል:: ለአብነት ያህል፤ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ኅብረት አባላት፤ ‹‹የአዲስ አበባን ጉዳይ እንዳንታዘብ ተከልክለናል›› ሲሉ ትዝብታቸውን ሰጥተዋል:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፤ በጉባዔው ላይ የአገዛዙን ስግብግብነት ለመሞገት የሞከሩ የራሱን ፓርቲ አባላት ጭምር፤ እያሳደደ መሆኑን የውስጥ ምንጮች እገለፁ ነው::

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ኅብረት ምክክሩን ለመታዘብ ገብቶ የነበረ ቢሆንም፤ የትዝብት ሪፖርቱን ነሐሴ 21 ቀን 2018 ዓ.ም ይፋ ሲያደርግ፤ አዲስ አበባን ጨምሮ በወሳኝ ጉዳዮች እንዳንታዘብ ተደርገናል ብሏል::

የዐብይ አገዛዝ ነውረኝነት፤ በሰብአዊ መብት ድርጅቶች ህብረት ላይ እገዳና ክልከላ በመጣል ብቻ አልተመለሰም:: በራሱ ሹመኞች ላይም ቁጣውን ገልጿል:: ለምሳሌ ከአማራ ክልል ተወክለን ያሉ የቡድኑን አባላት ሲገልጻቸውም፤ ‹‹ፋኖን ሰብስባችሁ ነው የመጣችሁት›› በማለት ሽመልስ አብዲሳ ዘልፏቸዋል:: ምክክር ተብየው፤ ከመፍትሔ ይልቅ በርካታ አሉታዊ እንቅስቃሴዎች፣ ሴራዎች፣ ዘለፋዎች፣ የታዩበት ነበር:: ይህም የዐብይ አሕመድ አገዛዝ፤ ያሰበውን ፀረ-ሕዝብ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ፤ ምንም አይነት የህግ፣ የፓርቲና የመንግሥት አሠራር እንዲሁም፤ ይሉኝታ የሌለው መሆኑን አስመስክሯል:: የዐብይ አሕመድ ወንጀለኛ አገዛዝ፤ በአዲስ አበባ ጉዳይ አማራው ብቻ የተቃወመው ለማስመሰል ጥረት ቢያደርግም፤ ከሁሉም ክልል መጥተው የተሳተፉት አዲስ አበባ በኦሮሚያ እንድትጠቀለል የሚተባበሩ አልነበሩም:: ይህን የዐብይ አሕመድና የአገዛዙን ድርጊት፤ ‹‹ከችርቻሮ ወደ ጅምላ›› የተደረገ እንቅስቃሴ እንደሆነ ይናገራሉ:: የምክክር ኮሚሽን የሚባለውን ተቋም ሲገልጹትም፤ ‹‹በሀገራዊ ምክክር ሽፋን ሀገር ለማፍረስ የተቋቋ ነው›› ብለውታል::

ምሁራኑ ሃሳባቸውን ሲያብራሩም፤ ቀደም ሲል በየቀኑ በሚወሰዱ መመሪያዎች፣ በመሬት ወረራ እና በህገ-ወጥ አሰራሮች "በችርቻሮ" ሲከናወን የቆየው አዲስ አበባን የመንጠቅ ሂደት፤ አሁን ላይ በገዢው ፓርቲ በተለይም በዐብይ አሕመድ ጥላ ስር በሚንቀሳቀሰው የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኩል፤ ሀገርን ለመሸጥ የታሰበ ትልቁ የታሪክ ወንጀል እንደሆነ ይገልፃሉ:: ጨፍጫፊው ዐብይ አሕመድ፤ ‹‹ለጋራ ችግራችን የጋራ መፍትሔ እንፈልግ›› ብሎ እንደተለመደው የማታለል ዘዴው፤ አዲስ አበባ ላይ የሰበሰባቸው የራሱ ተወካዮች ሳይቀሩ ሲቃወሙት፤ በብልጽግና ፓርቲ ውስጥ ያልተደራጁ እንደ ጃዋር መሀመድ፣ ፀጋዬ አራርሳ፣ መረራ ጉዲና፣ ቀጀላ መርዳሳ የመሳሰሉት የብሔሩ ምሁራን እና ፖለቲከኞች ግን፤ የዐብይ አሕመድን የሥልቀጣ ፍላጎት ወደመሬት ለማውረድ፤ ከሀገር አፍራሹ ዐብይ አሕመድ ጎን ተሰልፈው ታይተዋል::

የወለጋ/ቢዛሞ አማራን ጨፍጭፎ ለመጠቅለል የተነሳው የዐብይ አሕመድ አገዛዝ፤ ከዚህ እኩይ ድርጊቱ የሚመለስበት ብቸኛ መንገድ፤ ከሥልጣኑ ሲወገድ ብቻ ነው:: ዐብይ አሕመድና ለጭካኔ ማስፈጸሚያው ያደራጀው ቡድን፤ በተደራጀና በተቀናጀ ትግል ካልተወገደ የሚያደርሰውን አጠቃላይ ውድመት ማስረዳት፤ ለቀባሪ ማርዳት ነው::

አዲስ አበባ ዝም ብላ ለንግድ አመቺነት ወይም በወራሪዎች የተገነባች ከተማ አይደለችም:: ወይም ደግሞ የድንጋይና የኮንክሪት ስብስብ፤ ተራ የቆዳ ስፋት ያላት ከተማ ሳትሆን፤ የአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ከሁሉም በላይ ደግሞ የስነ-ልቦናዊ አንድነት ማዕከል ናት::

(ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል)

## ከሀገሪቱ ርዕሰ መዲና እስከ...

(ከገጽ 2 የቀጠለ)

ከተማዋ ለዘመናት የአድዋን ድል አክሊል ደፍታ፣ የአፍሪካ የነጻነትና የዲፕሎማሲ መዲና በመሆን የቆመችው፤ በውስጧ ባቀፈቻቸው በርካታ ብሔሮች፣ ሀይማኖቶችና ባህሎች የጋራ ድካም ውጤት ናት። አዲስ አበባ የሁሉም ብሔር ተወላጆች "የእኔም ቤት ናት" ብለው በሙሉ ስነ-ልቦናዊ ትስስር አምነውባት የሚኖሩባት የህብረ-ብሔራዊነት "ማቀላቀያ" (Melting Pot) ነች። አምባገነኑ ዐብይ አሕመድና ያደራጀው ስግብግብ ቡድን፤ አዲስ አበባን የአንድ ብሔር ብቻ ናት ብለው ሲነሱ፤ ይህ ሁሉ የህዝብ ግንኙነትና ትስስር፣ የባህልና የታሪክ ማህደር፣ አህጉራዊ አስተሳሳሪ ገመድ እና ዓለም አቀፍ ምልዶችን ሁሉ ለመበጣጠስ ነው የሚሠሩት።

በነገራችን ላይ ተስፋፊው ዐብይ አሕመድ ፍላጎቱ አዲስ አበባን በመሠልቀጥ ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። አንዳንድ የዐብይ ኦሮሞ ሰልቃጮች ሀገራዊ ምክክር ባሉት ጉባዔያቸው በድፍረት እንደተናገሩት አዲስ አበባ፣ድሬድዋ፣ ሀረርን፣ ጅጅጋን፣ ሀዋሳን ወዘተ የኦሮሚያ እምብርት ናቸው በማለት የዐብይ ኦሮሞ እምብርቷ የማያልቅ መሆኑን አሳይተዋል። ይህም የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በዐብይ ኦሮሞ የማይጨፈለቅ ከተማ፣ የማይፈናቀል ኢትዮጵያዊ እንደሌለ ከበቂ በላይ አስረጅ ነው።

ዘረ-ፈጁ ዐብይ አሕመድ እንደ ቀድሞው የማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ እብድ መሪ፤ ‹‹ጆን ቢዴል ቦካሳ›› በሥልጣን ሱስ የናወዘ እና ራሱን ከአንዲት የተከበረች አገር ጠቅላይ ሚኒስትርነት ይልቅ፤ እንደ ተራ ጦር አበጋዝ የሚያደርገው ወንበዴ እቅዱ በዚህ ደረጃ አገርን ማፍረስና ህዝብን መበተን መሆኑ ከቀን ወደ ቀን እየተረጋገጠ መጥቷል።

በአጠቃላይ፣ ዘረ-ፈጁ ዐብይ አሕመድና እሱ የሚመራው ፀረ አማራው ብልፅግና ፓርቲ፤ በአዲስ አበባ እየተገበረው ያለው አምባገነናዊና ሰልቃጭ ፖሊሲ፤ የከተማዋን ህብረ-ብሔራዊነት በመንጠቅ የአማራንና የሌሎችን ህዝቦች የፖለቲካና የስነ-ሕዝብ ሚዛን ለማዳከም የተነደፈ አደገኛ ፕሮጀክት ነው። አዲስ አበባን የፖለቲካ ቁማር መጫወቻ በማድረግ፤ የህዝብን የጋራ ቤት ማፍረስ፣ የኢትዮጵያዊነትን ስነ-ልቦና እና የጋራ ገመድ በመበጠስ አገሪቱን በቀጥታ ወደ መበታተን መንገድ መምራት ነው። ይህ ጉዳይ የሁሉም አገራዊና ህብረ-ብሔራዊ ኃይሎች የታሪክና የህልውና ኃላፊነት ሊሆን የሚገባው፤ ቀደም ሲል እንደገለጽነው፤ ይህንን አግላይና አደገኛ አካሄድ በጋራ በመመከት የአዲስ አበባንና የኢትዮጵያን የጋራ ባለቤትነት ማስከበር የመላው ኢትዮጵያዊ አሁናዊ ግዴታ ነው። ይህ የሚሳካው ደግሞ፤ በተቀናጀ፣ በተደራጀ፣ በተናበበ እና ለዓላማ በታመነ ሕዝባዊ ትግል በመታገል ነው።

## መቋጫ ሃሳብ፡

የአዲስ አበባ ጉዳይ የኢዲስ አበባ ነዋሪዎች ነው። የአዲስ አበባ ጉዳይ የመላ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ነው። ያለፉት ጥቂት ስርዓቶች የጋራ የሆነ ሀገራዊ እሴት ከመጨመር ይልቅ ትናንት በብዙ መሰዋእትነት በጋራ የሰራናቸውን ሀገራዊና ብሔራዊ ሀብቶቻችንና እሴቶቻችን እንደ ቅርጫ ስጋ መቀራመት ላይ እንቅልፍ አልባ እየሰሩ ነው። አንደ ኢትዮጵያ የቆምነው በጋራ በሰራናት አዲስ አበባ ነው፣ በጋራ አጥንትና ደማችን አፍስሰን አለምን ጉድ ያስባለ ጀብድ በፈፀምንበት አድዋ ነው። ካራማራ ላይ በጋራ በወደቅንበት በሰንደቁ ነው። የበታችነት በሽታ የሚያሰቃያቸው ራሳቸው አንሰው ሀገር ያሳነሱ፣ ሕዝብን ያኮሰሱ ደካማ መሪዎችና ድርጅቶች መጥተው ሁሉን ለእኔ የሆነ ኗላ ቀር አስተሳሰብ፣ የፋሽስት መንፈስ ተሸክመው ያለምንም ሀፍረትና የሞራል ተጠያቂነት አድዋም እነሱን ብቻ እንዲመስል፣ አዲስ አበባም የግላቸው እንደሆነ፣ በአባይ ግድብም ልዩ ጥቅም እንደሚያስፈልጋቸው የዘወትር አጀንዳቸው አድርገው አመጡ። ያለሀፍረት አብሮነትን አፈር አለበሱት፣ ሀገርን ሰላም ነሱ፣ ጅምላ ፍጅት አወጁ፣ የመጨራረስ ካርድ ሳቡ፣. . . ይህን ደም አፍሳሽ ስብስብ ከእኃ ርዕዮተአለሙ እንደ ድርጅት በፍጥነት ካልተወገደ ነገ ሁላችንም የለንም። ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ይህን ክፉ መንፈስ የተጠናወተው ስርዓት ተባብረን ዛሬውኑ እናስወግደው።

የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ ለእኩልነት፣ ለአብሮነት፣ ለፍትሕና ለጋራ ሀገር ግንባታ ይሰራል። ትግላችን የፍትህ ብቻ ሳይሆን የሕልውና ጭምር መሆኑ የየዕለት ውሏችን ህያው ምስክር ናቸው። ኑ አብረን ይህን ጉግማንጉግ ስርዓት እናስወገድና በፍቅር የምንኖርባት የጋራ ሀገር እንስራ። ገመቹም፣ ደስታም፣ ሀጎስም፣ ፋራህም፣ ሰዓዳም፣ ኦጁሉም፣ ገብረማርያምም፣ ሞሐመድም፣ አብረው በፍቅር የሚኖሩባት፤ ጥምቀትም፣ ኢድ አልፈጥርም፣ ኤሬቻም፣ ፍቼ ጨምበለላም፣ መስቀልም፣ አሸንድዬ/ሻደይም በነፃነትና በአብሮነት የሚከበሩባት ሕብረ-ብሔራዊት ሀገር እንስራ። ■

ህልውናችን በተባበረ ክንዳችን!

## "የነፃነት ድምጽ/ The Voice of Freedom"...

(ከገጽ 1 የቀጠለ)

### መጽሔቱ የሚይዛቸው ዋና ዋና ይዘቶች፤

- ❖ የአማራ ፋኖ የትግል መነሻ ምክንያቶች፣ የሚከተለው የትግል ስልትና ግቦች፣
- ❖ የአፋብን ድርጅታዊ ርዕዮተ-ዓለም እና የፖለቲካ ፕሮግራሞች:
- ❖ የፖለቲካ መምሪያው ሳምንታዊ ርዕሰ-አንቀጽ፣
- ❖ ሀገራዊ፣ ቀጣናዊና ዓለማቀፋዊ የፖለቲካ ትንታኔዎች፣
- ❖ አስተማሪ የሆነ የትናንት ታሪክ፣ የዛሬ እውነታና የነገ አቅጣጫ፣
- ❖ የሀሰት ትርክት ያላደበዘዘውና አምባገነኖች ያላጠፉት የአማራነት እውነት፣
- ❖ የሕዝባዊ የትግል ጥሪዎችና ወቅታዊ የፖለቲካ መልዕክቶች፣
- ❖ ወዘተ

### መፅሔቷን እንዴት ማግኘት እና ማሰራጨት ይቻላል፤

- ✓ በሳምንታዊ መጽሔቱ በዌብሳይት እና በማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ያገኛሉ፣
- ✓ በየአካባቢው በሚገኙ የንቅናቄው አስተባባሪዎች ጠይቆ ማግኘት ይቻላል፣

### የትግሉ ደጋፊዎች ንቁ ተሳትፎ አስፈላጊነት፤

- ❖ በየሳምንቱ በሚወጡ ጽሁፎች ላይ አስተያየትዎን በመፃፍ፣
- ❖ ጠቃሚ ግብዓቶችን ለዝግጅት ክፍሉ በመላክ፣
- ❖ በአካባቢዎ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በመጠቆም፣
- ❖ መጽሔቷን ለብዙሃኑ ተደራሽ በማድረግ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይገባል።

### የዝግጅት ክፍሉ፡

መጽሔቱ በፖለቲካ መምሪያው በሚደራጅ ዝግጅት ኮሚቴ የሚመራ ሲሆን የሚከተሉት አድራሻዎች ይኖሩታል፡

- ኢሜይል፤ contributions@thevoiceoffreedom.net
- ዌብሳይት፤ https://thevoiceoffreedom.net
- ቴሌግራም (ወደፊት ይተዋወቃል)፡
- ዋትስ አፕ (ወደፊት ይተዋወቃል)።

### ክፍል 2፡ የነፃነት ድምጽ ቁልፍ መርሆች፤

የነፃነት ድምጽ መጽሔት ከድርጅታችን አፋብንና ከፖለቲካ መምሪያው የተቀዱ የሚከተሉትን መርሆች ጠብቆ ይሰራል፡

1. **ማሕበራዊ እሴትን መጠበቅ፡** የአማራ ሕዝብ የዘመናት ታሪኩ እንደሚያሳየው ለአብሮነት የሚመች፣ ሰላም፣ ፍትህና እኩልነትን የሚሻ ሥልጡን ሕዝብ ነው። እንደሀገርም ከመገንጠል ይልቅ አብሮነትን፣ ከጎሳዊ እሳቤ ይልቅ ብሔራዊ አንድነትን፣ ከፅንፈኝነት ይልቅ አካታችነትና አብሮነትን ባሕሉ ያደረገ ሕዝብ ነው። በተጨማሪም የሀገር ማንነትና መገለጫ የሆኑ የጋራ የሕዝብ እሴቶች በአግባቡ መጠበቅ እንዳለባቸውም በጽኑ ያምናል። ለዚህም ተግቶ ይሠራል።
2. **የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት፡-** የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት፣ ሉዓላዊነትና፣ ብሔራዊ ጥቅም ሳይሸራረፍ መጠበቅ እንዳለበት በጽኑ ያምናል። ዜጎች ከማንኛውም የውስጥና የውጭ ወራሪ አደጋ ውስጥ እንዳይወድቁና ደህንጽቸው እንዲከበር ይሰራል።
3. **እኩልነትና ነፃነት፡-** ሁሉም የማሕበረሰባችን ክፍል ተከባብረውና ተሳስበው የሚኖሩባት ሀገር መኖር ለዘላቂ ሰላምና ፍትህ ቁልፍ ጉዳይ ነው። በሀገራችን ያሉ ብሔረሰቦች፣ ጎሣዎች፣ ሃይማኖቶች፣ ቋንቋዎች እና ባህሎች የሁላችንም እንደመሆናቸው መጠን፤ ተገቢው ዕውቅናና እንክብካቤ ሊደረግላቸው እንደሚገባ በጽኑ ያምናል።
4. **የኃይማኖትና የመንግሥት መለያየት፡-** መንግሥታዊ ኃይማኖት አይኖርም፤ ኃይማኖታዊ መንግሥትም አይኖርም። መንግሥት በኃይማኖት አሠራር ጣልቃ አይገባም፤ ኃይማኖትም በመንግሥት አሠራር ጣልቃ አይገባም። ሆኖም በትውልድ ግንባታ ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው በመሆኑ መንግሥት የሕዝቡን ነባር ባህሎች፣ ኃይማኖቶች እና እሴቶች እንዲጠበቁና እንዲከበሩ ይሰራል።
5. **በትብብር መሥራት፡-** የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ አንድ ወጥ አማራዊ ተቋም እንዲፈጠር አጥብቆ ይሠራል። በተጨማሪም ከማንኛውም ጭቆናንና ዘር

(ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል)

## "የነፃነት ድምጽ/ The Voice of Freedom"...

(ከገጽ 3 የቀጠለ)

ጭፍጨፋን ከሚቃወም፣ የአማራ ሕዝብ መሠረታዊ የትግል ምክንያቶችን ከሚያከብር፣ የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄን የትግል ግብ የሚያከብር እና ፍትህ ፈላጊ ከሆነ ድርጅት ጋር ተባብሮ ለመሥራትና ሀገራዊ መንግሥት ለመመሥረት ጽኑ ፍላጎት ያለው ተቋም ነው፡፡ ስለሆነም የነፃነት ድምጽ ይህን መርህ አክብሮ ይሰራል፡፡

6. **የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ማክበር፡-** የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ ለሰብዓዊ መብትቶች መከበር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ የሰው ልጆች የሰብዓዊነት መርሆች እንዲከበሩ የሚያስችሏቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደረጉ ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ መሠረታዊ የሆነው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (Universal Declaration of Human Rights) /UDHR/ ነው፡፡ የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ ይህን ድንጋጌና ሌሎች ዓለማቀፍና አህጉር አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕግጋቶችን በጽኑ የሚያከብር መሆኑን የነፃነት ድምጽ አጉልቶ ያሳያል፡፡
7. **እውነተኛ ትርክት መገንባት፡-** አማራ ለዚህ ሁሉ ግፍና በደል የተጋለጠው በተውሶና ፀረ-አማራ በሆነ ትርክት ነው፡፡ ስለሆነም የአማራ ትግል አንዱ ዓላማ፤ ይህን ስሁት ፀረ-አማራ ትርክት በእውነተኛ ትርክት በመቀየር፤ የአማራን ሕዝብ የሀገር ባለውለታነት፣ ሥልጡንነት፣ እውነተኛ ባህልና እሴቶች ባለቤትነት፣ እንደሀገር ለመቀጠል፣ ቀጠናውንም ሰላምና መረጋጋት ለመመለስ የአማራ እውነተኛ ትርክት በልኩ ሊነገር፣ በሁሉም ዘንድ ሰርጾ ሊሰራበት ይገባል፡፡ የተገንጣይና የጎሰኝነት ትርክት ታርሞ፤ እንደሀገር በጋራ ሊያስቀጥል የሚችል እውነተኛ ትርክት ሳይደበዝዝ ተቆጣጥሮ ማዝለቅ የክፍሉ ኃላፊነት ይሆናል፡፡
8. **ሕዝባዊነት፡-** የአማራ ፋኖ ትግል የግለሰቦች ወይንም የጥቂት ቡድኖች አይደለም፡፡ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ዋጋ የተከፈለበት የትውልድ ቅብብሎሽ ትግል ነው፡፡ ስለሆነም የአማራ ፋኖ ትግል ባለቤቱ የአማራ ሕዝብ ነው፡፡ የዚህ ትግል ታሪካዊ መሪ ደግሞ የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ ነው፡፡ ስለሆነም ባለአደራ የሆነው አፋብን ሚሊዮኖች ዋጋ የከፈሉለትን ይህን የአማራ ሕዝብ ትግል ቁልፍ የሆኑ ድርጅታዊ ውሳኔዎችና እጥፋቶችን በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ አባላትና ሕዝብን እያወያዩና እያማከረ የትግሉን ዓላማና ግብ የጠበቀ መሆኑን ያመላክታል፡፡
9. **ተአማኒነትና ግልፀኝነት፡-** የነፃነት ድምጽ የድርጅቱን የፖለቲካ ስራዎች ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ነው፡፡ ድርጅቱ የሚያሳልፋቸውን የፖለቲካ ውሳኔዎች፣ ስምምነቶች፣ የትግል ጥሪዎችና አቅጣጫዎች ለሕዝብና ለአባላት ግልጽ መሆን ያለባቸውን ግልጽ አድርጎ ያስቀምጣል፡፡

"እውነትን ማወቅ ለነፃነት የመጀመሪያው እርምጃ ነው!"
የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ – የፖለቲካ መምሪያ ■

## The Integrated State-Led Campaign to Dismantle the Nation... (continued from page 1)

Dictators and organizations afflicted by an inferiority complex, diminished in themselves, who have belittled the country and degraded the people—have arrived carrying a backward mindset that everything belongs to them, infused with the spirit of apartheid. Without any shame or moral accountability, they have made it their daily agenda to make Adwa resemble them, claim Addis Ababa as their private property, and demand special benefits regarding the Abay (Grand Ethiopian Renaissance) Dam. Shamelessly, they have dragged togetherness through the mud, robbed the nation of peace, declared mass slaughter, and drawn the card of mutual destruction...

If this bloodthirsty group, along with its ideology as an organization, is not removed swiftly, none of us will exist tomorrow. As the saying goes, "Extinguish the fire before the leaves burn"—let us unite today and eliminate this regime possessed by an evil spirit – before it destroys us all.

The Amhara Fano National Movement works for equality, togetherness, justice, and the building of a shared nation. Our daily reality bears living witness that our struggle is not only for justice, but for our very survival. Come, let us unite to remove this monstrous regime and build a shared country where we live in love and harmony. Let us build a multinational country where Gemechu, Desta, Hagos, Farah, Saada, Ojulu, Gebremariam, and Mohammed live together in love; where Epiphany, Eid al-Fitr, Irreecha, Fichee-Chambalaalla, Meskel, and Ashendye/Shadey/Ashenda are celebrated in freedom and togetherness. ■

## የ2019 የትምህርት ዘመንን በተመለከተ ...

(ከገጽ 1 የቀጠለ)

ከዚህም በላይ ላለፉት ሶስት አመት በላይ በአማራ ክልል ውስጥ በሚኖረው አማራ ይፋዊ መንግስታዊ ጦርነት በማወጅ በጅምላ እየተጨፈጨፈ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጦርነትም ባሻገር የሕክምና ተቋማት በአግባቡ አገልግሎት




እንዳይሰጡ በማድረግ ተላላፊ ለሆኑና ላልሆኑ በሽታ ተጋልጠው ታክመው እንዳይድኑ በማድረግ ማልማት የማይችል ማህበረሰብ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መጭው የአማራ ትውልድ በጦርነት ውስጥ ሆኖ የተረጋጋ የትምህርት እድል ማግኘት የማይችል በራሱ መንግስት የመከራ ቀንበር የተጫነበት ሕዝብ ነው፡፡ በተለይም ያለፉት ሶስት የትምህርት ዘመናት ትምህርት ቤቶችን የጦር ካምፕና የወታደር ምሽግ በማድረግ፣ የትምህርት ቤቶችን መሰረተልማትና ቁሳቁሶች ወድመዋል፡፡ በእቅድ አማራን ማጥፋት እየሰራ ያለው አገዛዝ ትምህርት ቤቶችን ሆን ብሎ በሞርታር፣ መድፍና አየር ኢላማ ሲያደርግ በመቆየቱ ምክንያት በርካታ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ ሆነዋል፡፡ ለትምህርት የደረሱ ወጣቶችን አፍሶ ለወታደራዊ ግዳጅ በመውሰድ እና በርካታ መምህራንን በፖለቲካ ሰበብ በማሰርና በማሸማቀቅ አጠቃላይ የትምህርት ሴክተሩ ሽባ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ድሮውንም በአካባቢው ቁሳቁስ ከዳስ ባልተሻለ ሁኔታ የተሰሩት በርካታ የገጠር ትምህርት ቤቶችም በጦርነትና በእንክብካቤ እጥረት ምክንያት ወደ ፍርስራሽነት ተቀይረዋል፡፡ ቀደም ሲል በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ሲቋረጥ የነበረው የትምህርት ፕሮግራም ባለፉት ሶስት አመት ግን በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአማራ ልጆች የትውልድ ብርሃን ከሆነው የትምህርት ገበታ ውጭ ሆነው ቆይተዋል፡፡ ይህ ዘረፈጅ ጦርነት አሁንም እንዲሁ እንደሚቀጥል የአገዛዙን ትክክለኛ እቅድና እንቅስቃሴ የተገነዘበ ሁሉ የሚያውቀው ሃቅ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በውሉ የገመገመው የአማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ እጅግ በማይመች ሁኔታም ሆነው ለትምህርት የደረሱ ወጣቶች ወደ ትምህርት መስጫ ማዕከላት በመሄድ የአካባቢው ሁኔታ የፈቀደውን ትምህርት ለመማር መወሰን እንደሚገባ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡
ምንም እንኳን ሁኔታው የጦርነት ቀጠና፣ የመማሪያ ክፍሎች የሌሉበት፣ የተሟላ መምህራን የማይገኙበት፣ የመማሪያ ቁሳቁስ የወደመበት፣ በየቦታው አማራው በጅምላ እየተገደለና እየተሳደደ የህልውና አደጋው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ ያለበት ቢሆንም ትምህርት ቤት አለመዋሉ በቀላሉ የማይስተካከል ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቦናዊ ቀውስን በትውልዱ ላይ ፈጥሯል፡፡ ስለሆነም በምንም ሁኔታ ውስጥ ሆነን ልጆቻችን ለስነልቦናቸው ትምህርት ቤት ዋልን የሚል አእምሮ እንዲኖራቸው ይፈለጋል፡፡ አለም በትምህርትና በምርምር በመራቀቅ ልዕልና ላይ ደርሶ የትውልድ እሽቅድድሞች በሆነበት ዘመን ደመኛ አገዛዝ የገጠው የአማራ ትውልድ ጨርሶ እንዳይመክን ቢያንስ ትምህርት ቤት ይዋሉ፡፡
ስለሆነም ወላጆች፣ መምህራን፣ ሰብአዊ ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ተቆርቋሪዎች፣ አለማቀፉ ማህበረሰብ ሁሉ በመረባረብ ትውልዱ ነገ ጨረሶ እንዳይጨልምበት የትምህርት ጭላንጭል ባለበት ሁሉ እንዲውል ትብብር ያድርግ፡፡
ከዚህ በፊት ትምህርት የጀመርንም ሆነ ላለፉት ሶስት ተከታታይ አመታት አቋርጠው የነበሩ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የጎደለውን ተረባርበን እንደማህበረሰብ ተደጋግፈን በመጠገን ትምህርት እንዲጀመር ጥሪት እናድርግ፡፡
የምዝገባና የትምህርት ማስጀመሪያ መርሃ ግብርን በተመለከተ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ስለሚኖራቸው ተሳትፎና ትብብር የስራ አቅጣጫ በተመለከተ የአፋብን ማሕበራዊ ጉዳዮች መምሪያ በየዕዞቹ በሚያወርደው አቅጣጫ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን ለመጠቆም እንወዳለን፡፡

የትውልዱ ነገ እንዳይጨልም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ትምህርት ለማስቀጠል ርብርብ እናድርግ! ■